የሰ/መ/ቁ. 53985

ህዳር 13 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ዳሽን ባንክ አ.ማ ነ/ፈጅ የሺወርቅ ይመር ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ዘነበ ድንቄሣ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 "ን" መሠረት ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- በአመልካች ድርጅት ውስጥ ላይ በማገልገል ላይ እያሉ በጋዜጣ ላይ አስተያየት ሰጥተሃል በሚል ሰበብ አመልካች ድርጅት ከታህሳስ 14 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ ያላግባብ ከሥራ ያገዳቸው መሆኑን በመግለጽ ወደ ሥራ እንዲመለሱ የታህሳስ ወር ደመወዝ ከተለያዩ ወጪና ኪሳራዎችጋር እንዲከፈላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም ተጠሪ በአመልካች ላይ ከባድ ጉዳት እያደረሱ በመሆኑ ጉዳዩ እስኪጣራ ድረስ ከስራ መታገዳቸውን ገልፆና እግዱም በአግባቡ የተሰጠ መሆኑን ጠቅሶ እግዱ ሊነሳ አይገባውም ሳልሰሩበት ጊዜ ደመወዝ ሊከፈላቸው እንደማይገባ ገልጾ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዮን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም አመልካች ተጠሪን ከስራ ያገዳቸው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 18 መሠረት ለማገድ የሚያበቁ ሕጋዊ ምክንያቶች በሌሉበት ሁኔታ መሆኑን ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የአዋጅ አንቀጽ 27(4) ድንጋጌ ሲታይም እግድ የሚፈቀደው በሕብረት ስምምነት ላይ በተመለከተው መሰረት መሆኑን ገልፆ ሕብረት ስምምነቱ በሌለበት ሁኔታ ተጠሪን አመልካች ከሥራ ማገዱ ሕገ ወጥ ነው በሚል ድምዳሜ ተጠሪን የታህሳስ ወር 2002 ዓ.ም ደመወዝ በመክፈል አመልካች ወደ ሥራ እንዲመለስ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ መጋቢት 06 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፉት የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(4) ድንጋጌ ጥፋት መኖሩን አሰሪው

እስከሚያጣራ ድረስ ሰራተኛን ከስራ በማገድ ጉዳዩን ለማጣራት የሚችል መሆኑን ፈቃጅ በሆነ አገላለጽ ደንግጎ እያለ የሕብረት ስምምነት ከሌለ ተፈጻሚነት የለውም በሚል የአመልካች እርምጃ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ በመታዘዙ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው መስከረም 10 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅም ጥቅምት 10 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ተጠሪን ከስራ እና ደመወዝ ያገዳቸው ተጠሪ በድርጅቱ ላይ ጉዳት እያደረሱ ነው በሚል ጉዳዩን እስከሚያጣራ ድረስ ሲሆን ለእርምጃው ህጋዊነት በዋቢነት የሚጠቅሰውም አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/(4) ስር የተመለከተውን መሆኑን ሲሆን የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን እርምጃ ሕገ ወጥ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሱት ሕብረት ስምምነት ሳይኖር በአዋጁ አንቀጽ 27(4) ስር የተመለከተው ድንጋጌ ተፈጻሚነት የለውም በሚል ምክንያት መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ችሎት የሕግ ትርጉም የሚያስፈልገው ነጥብ የሕብረት ስምምነት የሌለው አሠሪ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(4) መሠረት የማገድ እርምጃ መውሰድ አይችልም ተብሎ በበታች ፍርድ ቤቶች መወሰኑ ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

በመሠረቱ የቅጥር ውል ባይቋረጥም አሰሪውና ሰራተኛ ከግዴታዎቻቸው ለተወሰነ ጊዜ ነፃ የሚሆኑባቸው ሁኔታዎች ያሉ ስለመሆኑ አዋጁ ቁጥር 377/96 ከአንቀጽ 17 እስከ 22 ድረስ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ የቅጥር ውል ሲታገድ ምክንያቶቹ የተለያዩ ሊሆኑ እንደሚችሉ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎችና ከአንቀጽ 27(4) እና 184 ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡ ለአሁኑ ጉዳይ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው የእገዳ አይነት በአዋጁ አንቀጽ 27(4) ስር የተመለከተው ከዲስፕሊን ጋር ተያይዞ የሚፈፀምና የስራ ውልን ለማቋረጥ የሚያስችሉ ጥፋቶችን ለማጣራት የሚደረግ እገዳ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት በአንቀጽ 27 ስር በተመለከቱት ምክንያቶች መሠረት የስራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ እንዲቋረጥ ከመደረጉ በፊት ሰራተኛውን ለአንድ ወር ያህል ከስራ አግዶ ማቆየት ስለሚቻልበት ሁኔታ በህብረት ስምምነት ሊወሰን ይችላል ተብሎ ተደንግጓል፡፡ የድንጋጌው ዓይነት ዓላማ አሰሪው በአስተዳደራዊ ሥልጣኑ ሰራተኛው ለሚፈጽመው ጉድለት ተገቢውን የዲሲፕሊን እርምጃ ለመውሰድ ይችል ዘንድ ሠራተኛው ፈፀመ የተባለውን የሥነ ምግባር ጉድለት በተገቢው መንገድ ለማጣራትና ለመመርመር እንዲችል ማድረግ ነው፡፡ ሕጉ ይህንን አላማ ለማሳካት ይቻል ዘንድ እገዳ ማድረግን የሚፈቅድ ሲሆን እገዳው የሚቆይበትን የጊዜ ገደብም ከአንድ ወር መብለጥ እንደሌለበት ያስቀምጣል፡፡ ሕጉ አሰሪው እገዳውን ሲፈጽም ከድርጅቱ ሰራተኛ ማህበር (በህብረት ስምምነት መሠረት) ጋር በመስማማት ለመወሰን እንደሚችል ያሳያል፡፡ ሆኖም የህብረት ስምምነት የሌለው ድርጅት ሰራተኛውን ቢያግድ እገዳው ሕገ ወጥ ሊባይ ሚችል ስለመሆኑ የድንጋጌው ይዘትና አቀራረጽ አያሳይም፡፡ የእገዳው አላማ በሰራተኛው ተፈፀመ የተባለውን የስነ ምግባር ጉድለት በተገቢው መንገድ ማጣራትና ለመመርመር አሰሪውን ለማስቻል ነው ከተባለ የሠራተኛ ማህበር የሌለው (የሕብረት ስምምነት (የሌለው) ድርጅት ሰራተኛው ፈፀመ ለተባለ ጉድለት እገዳ በማድረግ የዲስፕሊን ግድፈቱን ለማጣራት ወይም ለመመርመር አይችልም የሚባልበት ሕጋዊ ምክንያት

የለም፡፡ ድንጋጌው በይዘቱ ሲታይ ፈቃጅ እንጂ ክልከላ ያበጀ አይደለም፡፡ አገዳው የሚደረግበት አላማ ሲታይ እውነቱ በትክክል እንዲወጣ በሕጋዊ ምክንያት የስራ ውል እንዲቋረጥ ለማድረግ፣ ሰራተኛውም ለአሰሪው ታማኝ በመሆን አገልግሎቱን እንዲሰጥ በማድረግ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ እንዲሁም የኢንዱስትሪ ሰላምን ማስፈን ነው፡፡ ሕግ ሲተረጎምም ይህንን ግንዛቤ ውስጥ ባስገባ መልኩ መሆን እንዳለበት ተቀባይነት ያላቸው የሕግ አተረጓጎም ደንቦች የሚያስገነዝቡን ሐቅ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ሕግ ሊተረጎም የሚገባው የሕጉን አላማ በሚያሳካ መልኩ ስለመሆኑ የሕግ አተረጓጎም መርሆዎች ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም አንድ የሕብረት ስምምነት የሌለው አሰሪው ሰራተኛው የዲስፕሊን ጉድለት ፈጽሟል የሚልበትን ጉዳይ ለማጣራትና ለመመርመር ሰራተኛውን ከአንድ ወር ጊዜ ላልበለጠ ጊዜ ቢያግድ እርምጃው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(4) የሚሸፈን አይደለም የሚባልበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ የሰጡት ውሳኔ መሠታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 48933 ጥር 19 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 89046 መጋቢት 01 ቀን 2002 ዓ/ም በትእዝዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የህብረት ስምምነት ባይኖረውም ተጠሪ ፈፀሙ የተባሉትን ድርጊት ለማጣራት ወይም ለመመርመር በአዋጁ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(4) መሠረት ለአንድ ወር ጊዜ ያህል ማገድ ይችላል ብለናል፣ አገዳው ተነስቶ ተጠሪን ወደ ስራ ይመልስ ተብሎ ሊገደድ አይገባም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ